**ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ**

በአሁኑ ወቅት አገራችን የምትገኝበት የህልውና አደጋ በእጅጉ ያሳሰበን ኢትዮጵያውያን ራሳችንን “የኢትዮጵያ ህልውና ተቆርቋሪዎች ስብስብ (ኢህተስ)” በሚል ጊዜያዊ መጠሪያ በማሰባሰብ በአገራችን እየተካሄደ የሚገኘው ጦርነት በአስቸኳይ እንዲቆምና ህዝባችንን ከተጨማሪ እልቂት፣ አገራችንን ከመበታተንና ከመፈራረስ የሚታደግ አማራጭ የሰላም ሃሳብ ለማቅረብ ጥረት ስናደርግ ቆይተናል። በወራት ለሚቆጠር ጊዜ በአገር ውስጥና በውጭ ከሚኖሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን ጋር የሃሳብ ምክክርና ወይይት ካደረግን በኋላም ይህንን ለውይይትና ለድርድር ሂደት መነሻ ሊሆን የሚችል የሰላም አማራጭ ሃሳብ ይዘን ለመቅረብ በቅተናል።

ይህ፣ “ተኩስ ይቁም! ሃቀኛ ውይይትና ድርድር ይካሄድ! ሁሉን አቀፍ የሽግግር ሂደት ይጀመር!” በሚሉ ሶስት የማይነጣጠሉ ሀይለ-ሃሳቦች ላይ የሚያጠነጥነው አማራጭ ሃሳባችን ቢያንስ በመነሻ አማራጭ ሃሳብነት በተፋላሚ ወገኖች ዘንድ ተቀባይነት ቢያገኝና ቢተገበር ህዝባችንን ከሚገኝበት የእለት-ተእለት ሰቆቃ፣ አገራችንን ከአጠቃላይ ውድመትና ጥፋት የመታደግ እድል ይፈጥራል የሚል ጽኑ እምነት አለን። ስብስባችን በብዙ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የተለያየ አመለካከት የምናራምድ ዜጎችን ያካተተ ቢሆንም አገራችን በአሁኑ ወቅት ከገባችበት የፖለቲካ ቀውስ ልትወጣ የምትችለው ግን ከሞላ ጎደል በእዚህ የሰላም ሰነድ ላይ የቀረቡትን ሚዛናዊ አማራጭ ሃሳቦች በመቀበልና በመተግበር ነው የሚል የጋራ መግባባት ላይ ደርሰናል። ስለሆነም ለኢትዮጵያ ህልውና መቀጠል ተቆርቋሪ የሆናችሁ ዜጎች ሁሉ፤ ይህ አማራጭ የሰላም ሃሳብ በተፋላሚ ወገኖች ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝና በአስቸኳይ ሰላማዊ የውይይትና የድርድር ሂደት እንዲጀመር የየበኩላችሁን ግፊት እንድታደርጉ ስብስባችን በአክብሮት ይጠይቃል።

የኢትዮጵያ ህልውና ተቆርቋሪዎች ስብስብ

ህዳር 2014 ዓ. ም.

**ተኩስ ይቁም !**

***ሃቀኛ ውይይትና ድርድር ይካሄድ !***

***ሁሉን አቀፍ የሽግግር ሂደት ይጀመር !***

ኢትዮጵያን ከጥፋት ለመታደግ ለውይይት የቀረበ የሰላም መነሻ ሃሳብ

(ከኢትዮጵያ ህልውና ተቆርቋሪዎች ስብስብ፤ ህዳር 2014 ዓ.ም.)

***መግቢያ***

*አገራችን ኢትዮጵያ እጅግ አደገኛ በሆነ የእርስ-በእርስ ጦርነት ውስጥ በመዘፈቋ ምክንያት በታሪኳ አይታው በማታውቀው መጠን አለም አቀፍ መነጋገሪያ ከሆኑ ጥቂት አገሮች መካከል አንዷ ሆናለች፡፡ ቀድሞውኑ የፓርቲ ውስጣዊ ልዩነቶቻቸውን በሰላማዊ መንገድና ብስለት በተሞላበት ሁኔታ ሊፈቱ ሲገባቸው በሃላፊነት ስሜት ራሳቸውን መግራት የተሳናቸው ሃይሎች የለኮሱት ይህ ጦርነት የታጣቂ ሃይሎችን ብቻ ሳይሆን የብዙ ሲቪል ዜጎችን ህይወት በየቀኑ እየቀጠፈ፣ ኢኮኖሚውን እያወደመ፣ በአጠቃላይም አገራችንን ወደ መተላለቅና የመፈራረስ አደጋ በፍጥነት እየገፋት ይገኛል፡፡ እነሆም ጦርነቱና ዳፋው ከኢትዮጵያ አልፎ የአካባቢው አገራትና የአለም አቀፉ ህብረተሰብ የደህንነት ስጋት የመሆን ደረጃ ላይ በመድረስ ተባብሶ ቀጥሏል። የፖለቲካ መሪዎች ግብዝነት፣ በተለያዩ ፍላጎቶቻቸው የተነሳ ጦርነቱ እንዲቀጥል የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ግፊት፣ እንዲሁም የአለም አቀፍ ማህበረ-ሰቡ ዳተኝነት ለችግሩ አፋጣኝ ሰላማዊ መፍትሄ እንዳይገኝ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል። በተገቢው ጊዜና ሁኔታ በብቃት ተደራጅቶ ለመታገል ባለመቻሉ ምክንያት አገራችን ወደ እዚህ አይነት ፈተና እንድትገባ የበኩሉን አሉታዊ ድርሻ ያበረከተው የአንድነት የፖለቲካ ሃይልም ችግሩን ይበልጥ ከማባባስና ከማወሳሰብ ባለፈ ኢትዮጵያን ከህልውና አደጋ ለመታደግ አልቻለም።*

*በዚህም ምክንያት ላለፉት ሶስት አመታት ኦሮሚያን፤ ላለፈው አንድ አመት ትግራይን ሲያነድ የነበረው ጦርነት ካለፉት ጥቂት ወራት ወዲህ ደግሞ የአማራና የአፋር ክልሎችን እየለበለባቸው ይገኛል፡፡ ትናንት በትግራይ ሲሆን እንደታየው ዛሬ ሰሜን ጎንደር፣ ወሎና አፋር የእልቂት አውድማ ሆነዋል። ችግሩ መፍትሄ እስካላገኘ ድረስ ነገ ደግሞ ሌሎቹም የአገራችን ክፍሎች የሰቆቃው ተረኞች ሆነው ይቀጥላሉ። ይህ አውዳሚ ጦርነት ለአንድ ተጨማሪ ቀን በተራዘመ ቁጥር ችግራችን ይበልጡን እየተባባሰ፣ መፍትሄውም በእጅጉ እየራቀን የሚሄድ ሲሆን፣ ለተጨማሪ ወራት ወይም አመታት የሚካሄድ ከሆነ ደግሞ አገር ተረካቢውንና ተተኪውን ትውልድ የሚያሳጣን ከመሆኑም በላይ እንደ አገር የመቀጠል እድላችንንም ሊነፍገን ይችላል፡፡*

*በስልጣን ላይ የሚገኘው መንግስትም ሆነ ከእርሱ በተጻራሪ የቆሙ አማጺ ሃይሎች የችግሩ መፍትሄ መስሎ የታያቸው ጦርነቱን ማስቀጠልና አሸናፊ ሆኖ መውጣት ቢሆንም፣ የትኛውም ወገን የማሸነፍ እድል ቢያገኝም እንኳ ለአገራችን ዘላቂና አስተማማኝ መፍትሄ ሊያመጣ ከቶ አይችልም፡፡ የወቅቱን የፖለቲካ ቀውስ መፍታት የሚቻልበት ብቸኛ መንገድ አሸናፊና ተሸናፊ በመሆን ሳይሆን በሰላማዊ የውይይትና የድርድር መንገድ የጋራ አሸናፊ ለመሆን በሙብቃት ነው። በእኛ እምነት ዘላቂነት ያለው ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው የሰላም አማራጭ የወቅቱን ጦርነት በማቆም አገራዊ የውይይትና የድርድር ሂደት መጀመርና ሁሉም የአገሪቱ የፖለቲካ ሃይሎች በአግባቡ የሚወከሉበትና የሚሳተፉበት ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግስት ማቋቋም ነው፡፡*

*ይህንን አላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ ከተለመደው ስልጣንን በብቸኝነት የመቆጣጠር እሳቤ በመላቀቅና ከሌሎች ጋር የስልጣን ተጋሪ ለመሆን በመወሰን የራስንም ሆነ የአገርን ህልውና ከጥፋት መታደግ ብልህነት ይሆናል፡፡ ከእዚህ አንጻር ሊወሰድ የሚገባው ጠቃሚ ትምህርት ቢኖር ከ1983 ዓ.ም. የሽግግር ሂደት በተለየና በተሻለ ሁኔታ ህጋዊነትንና ህዝባዊ ቅቡልነትን አጣምሮ የያዘ ሃቀኛና ሁሉን አቀፍ የሆነ አዲስ የሽግግር ሂደት መጀመር ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑ ነው። በእርግጥም ካለፉት ትውልዶች በተለየ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ መጻፍ ካለብን ከይስሙላ ምርጫ በተገኘ ህጋዊነትም ሆነ በጠመንጃ ሃይል አሸናፊነት ከሚገኝ ጊዜያዊ የበላይነት መመካትን ማቆምና ሁላችንም የጋራ አሸናፊ ለመሆን የምንበቃበትን የሰላም ጎዳና መምረጥና ማስቀደም ይኖርብናል።*

በመካሄድ ላይ የሚገኘው ጦርነት በምን አይነት ስምምነት ሊቋጭ ይችላል? በኢትዮጵያ ሊካሄድ የሚገባው የውይይትና የድርድር ሂደትም ሆነ ሊቋቋም የሚገባው የሽግግር መንግስትስ እንዴትና በእነማን ሊቋቋም ይችላል? ሂደቱ በምን አይነት መርህ ሊመራና ግቡስ ምን ሊሆን ይገባል? የሚሉት ጥያቄዎች በዝርዝር መመለስ የሚገባቸው በሂደቱ ተሳታፊና ተደራዳሪ በሚሆኑት ባለድርሻ አካላት እንደሆነ ግልፅ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በጥቅሉ ችግሩ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ሃሳብ ከማቅረብ ባለፈ ተጨባጭ የሆነ የመፍትሄ አማራጭ መኖሩን ለማመላከት በሚያስችል መጠን ብቻ ዘርዘር ያሉ አመላካች ሃሳቦች በዚህ ጽሁፍ ላይ እንዲቀርቡ ተደርጓል። ሆኖም የሰነዱ አላማ ከጦርነት የተለየ አማራጭ የሰላም ሃሳብ መኖሩን ለማመላከት ተብሎ የቀረበ በመሆኑ እነዚህ አመላካች ሃሳቦች ለመሻሻልም ሆነ ለመለወጥ ክፍት መሆናቸውን አስቀድመን ማስገንዘብ እንወዳለን።

ጦርነቱ እንዲቆምና ዜጎቻችን ከተጨማሪ እልቂት እንዲድኑ፣ በዘላቂነትም የኢትዮጵያ ህልውና ተጠብቆ እንዲቀጥል ፍላጎት ያላችሁ ቅን ዜጎች በሙሉ ይህን መነሻ ሃሳብ በቅንነት በመተቸትና በማዳበርም ሆነ ተፋላሚ ወገኖችና መንግስት እንዲቀበሉት ግፊት በማድረግ የየበኩላችሁን አስተዋጽኦ ታበረክቱ ዘንድ በዚህ አጋጣሚ ጥሪያችንን እናቀርባለን። በወቅቱ የሚታየው የኢትዮጵያ ቀውስ በውይይትና በድርድር እንዲፈታ ሃሳብ እያቀረባችሁ የምትገኙ የውጭ መንግስታትና ተቋማት ይህ የመነሻ ሃሳብ የአገራችንን ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ በአግባቡ በሚረዱና ለማንኛውም ተፋላሚ ወገን ሳይሆን ለአገሪቱና ለህዝቡ የጋራ ጥቅምና ደህንነት ብቻ ወገንተኛ በሆኑ ዜጎች ተዘጋጅቶ የቀረበ አገራዊ የሰላም ሃሳብ መሆኑን በመገንዘብ በየበኩላችሁ ለምታደርጉት ጥረት እንደ አንድ ጠቃሚ ግብአት ብትጠቀሙበት ተገቢ ነው እንላለን።

## 1. ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግስት ማቋቋምን አስፈላጊና ተመራጭ የሚያደርጉ አገራዊ ሁኔታዎች

ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግስት ማቋቋም ብቻ እንጂ ከዚህ ያነሰ ማናቸውም ጥገናዊ መንገድ በአሁኑ ጊዜ ለገጠመን የፖለቲካ ቀውስ መፍትሄ ሊሆን አይችልም ብለን እንድናምን ያስገደዱን ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. በእዚህ ጦርነት በዋናነት አሸናፊ ሆነው ለመውጣት እየተፋለሙ የሚገኙት ብልጽግና ፓርቲና ህወሃት የአገራችንን ህልውና አስጠብቀው ለማስቀጠል የሚያስችል ብቃት እንደሌላቸው ባለፉት ሰላሳ አመታት የአገዛዝ ዘመናቸው ከበቂ በላይ የተረጋገጠ በመሆኑ፤ በተጨማሪም ላለፉት ሶስት አመታት በስልጣን ላይ የሚገኘው ብልፅግና ፓርቲም በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ተስፋ ተጥሎበት የነበረውን የለውጥ ሂደት እንዲከሽፍ ማድረጉ፤

ለ. በአሁኑ ወቅት አገሪቱ ከፍተኛ የህዝብ እልቂትን፣ አሳሳቢ የኢኮኖሚ ውድመትን፣ አስፈሪ ረሃብን ያስከተለና ከዚህም በላይ በአጠቃላይ ኢትዮጵያን የህልውና አደጋ ላይ የጣለ የእርስ-በእርስ ጦርነት ውስጥ መግባቱ፤ ይህ ጦርነት ወደፊት ከቀጠለም አገራችን በፍጥነት መንግስት የለሽ ወደመሆንና የመፈራረስ አደጋ ውስጥ የመግባት እድሏ ሰፊ መሆኑ፤

ሐ. ጦርነቱ ቀጥሎ ዋና ተፋላሚ ከሆኑት ሀይሎች መካከል (ከብልፅግናና ከህወሃት) አንዳቸው አሸናፊ የመሆን እድል ቢያገኙ እንኳ ኢትዮጵያ ካለፉት ሰላሳ ዓመታት በተለየ አዲስና የተሻለ ስርአት የማግኘት እድል የሌላት መሆኑ፤

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የምትገኝበት ወቅታዊ ሁኔታ እጅግ ውስብስብ፣ አሳሳቢና መሰረታዊ በሆኑ ፈርጀ ብዙ ችግሮች የተተበተበ በመሆኑ ምክንያት ችግሩ አሁን በሚገኝበት ደረጃ በስልጣን ላይ በሚገኘው የብልፅግና መንግስት ብቸኛ አመራርም ሆነ ሁሉን አቀፍ ከሆነ የሽግግር መንግስት ከማቋቋም ባነሰ ማናቸውም አይነት መንገድ መፍትሄ ሊያገኝ አይችልም ከሚል መደምደሚያ የሚነሳ የሰላም ሃሳብ ነው፡፡

## 2. የእርስ በእርስ ጦርነቱን በዘላቂነት ለማስቆም ይቻል ዘንድ በቅደም ተከተል ሊፈጸሙ የሚገባቸው መፍትሄዎች

ኢትዮጵያ የምትገኝበት የፖለቲካ ቀውስ እጅግ ወስብስብና ፈርጀ ብዙ በሆኑ ተደራራቢ ምክንያቶች የተከሰተ በመሆኑ በአንድ ቀላልና አቋራጭ መንገድ ሊፈታ የሚችል አይደለም። ከችግሩ ክብደትና ውስብስብነት ጋር የሚመጣጠን ሁሉን አቀፍና ሁሉንተናዊ የሆነ መፍትሄ ያሻዋል። በእኛ እምነት ችግሩን ዘላቂና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ለመፍታት ቢያንስ የሚከተሉትን አራት መሰረታዊ ሂደቶች መፈጸም ያስፈልጋል።

ሀ. በቅድሚያ በጦርነቱ ውስጥ የሚገኙና አስቸኳይ የምግብና የመድሃኒት እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን አካባቢዎች ተደራሽ ማድረግ፤

ለ. ከተፋላሚ ወገኖች የድርድር ስምምነት የሚመነጭ የተኩስ ማቆም እርምጃ መውሰድ፤

ሐ. በመሰረታዊ አገራዊ የፖለቲካ ችግሮች ዙሪያ ቀጣይነት ያለው አገራዊ የውይይትና የድርድር (National Dialogue) ሂደት መጀመር፤

መ. ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግስት ማቋቋም፤ ናቸው፡፡

በ "ሀ" ላይ የሰፈረው ነጥብ (አስቸኳይ የምግብና የመድሃኒት እርዳታን የሚመለከተው ጉዳይ) ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ አንገብጋቢ ጉዳይ በመሆኑ ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታ ማቅረብም ሆነ ድርድር መጀመር ሳያስፈልግ ሁሉም ተፋላሚ ወገኖች ሁሉንም የጦርነት አካባቢዎች ለእርዳታ ስርጭት በአስቸኳይ ክፍትና ተደራሽ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በ "ለ" ላይ የሰፈረውና የተኩስ ማቆም ስምምነትን የሚመለከተው ሂደት ሊተገበር የሚችለው ጦርነቱ አሁን በደረሰበት ደረጃ እንዲቆም ከተደረገ ብቻ ነው። በተቃራኒው ጦርነቱ ከቀጠለና በተፋላሚ ወገኖች መካከል አንዱ ሙሉ ለሙሉ በሚባል መጠን ጦርነቱን አሸናፊ ለመሆን ከበቃ ሊተገበሩ የሚችሉት በ "ሐ" እና በ "መ" ላይ የሰፈሩት ሁለት ሂደቶች ብቻ እንደሚሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ ለአገሪቱ ጠቃሚ የሚሆነው አማራጭ ጦርነቱን ባለበት ደረጃ ለማቆም መስማማትና በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ተጨማሪ ዜጎችን ህይወት መታደግ ነው። አሸናፊና ተሸናፊ ከመሆን በፊት ጦርነቱን በስምምነት ለማቆም መቻልም በአገሪቱ ሚዛናዊ የፖለቲካ የሃይል አሰላለፍ እንዲኖር ለማድረግና በሚቋቋመው የሽግግር ሂደት እንደ 1983ቱ ዓ.ም. አንድ የፖለቲካ ሃይል የበላይነት እንዳይኖረው በማድረግ ረገድ አስተውጽኦ እንደሚኖረው መገንዘብ ያስፈልጋል።

## 3. ውጤታማ የተኩስ ማቆም ስምምነት ላይ ለመድረስ ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባቸው ጉዳዮች

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ በጦርነትም ሆነ በረሃብ እያለቀ የሚገኘውን ህዝብ ከባሰ አደጋ ለመታደግም ሆነ ለችግሩ ዘላቂና አስተማማኝ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል የውይይትና የድርድር ሂደት ለመጀመር በዋና ቅድመ ሁኔታነት ሊወሰድ የሚገባው እርምጃ ጦርነቱን በአስቸኳይ ማቆም ነው። ጦርነቱን ለማስቆምም የሚከተሉትን መሰረታዊ ነጥቦች በቅደም ተከተል መተግበር አስፈላጊ ይሆናል።

ሀ. በቅድሚያ በስልጣን ላይ የሚገኘው መንግስት የወቅቱን አገራዊ የፖለቲካ ችግር በሰላማዊ መንገድና ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግስት በማቋቋም ለመፍታት የወሰነ መሆኑን በማሳወቅ ለሁሉም ተፋላሚ ወገኖች ግልጽ የሆነ የተኩስ ማቆም ጥሪ ሊያቀርብ ይገባል፡፡ የመንግስትን ጥሪ ተከትሎ ሁሉም ተፋላሚ ወገኖች በያሉበትና በተናጠል ተኩስ ማቆማቸውን በይፋ ሊያሳውቁ ይገባል፡፡ እዚህ ላይ መንግስት ቀዳሚውን ተነሳሽነት እንዲያሳይ የተፈለገው የህዝቡን ሰላምና ደህንነት የማስከበር የበለጠ ሃላፊነት ያለበትና በተግባርም ለውጥ ለማምጣት የተሻለ እድል የሚኖረው መንግስት ነው ከሚል ምልከታ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ለ. ተፋላሚ ወገኖች የተናጠል የተኩስ ማቆም እርምጃ በወሰዱ ጥቂት ቀናት ውስጥ የጋራ አደራዳሪ አካላትን የመምረጥ ድርድር ሊጀምሩ ይገባል፡፡ በእዚህ ረገድ የሚደረገውን ድርድር ተፋላሚ ወገኖች በአካል መገናኘት ሳያስፈልጋቸው በያሉበት ሆነው ሊያካሂዱት ይችላሉ።

ሐ. ተፋላሚ ወገኖች የጋራ አደራዳሪ አካላትን ከመረጡ በኋላ አሉን የሚሏቸውን የመደራደሪያ ነጥቦች ይዘው ድርድር መጀመርና በመጨረሻም ዘላቂ የተኩስ ማቆም ስምምነት ሊፈራረሙ ይገባል፡፡

መ. አደራዳሪዎች ከተቻለ ከአገር-በቀል ተቋማትና ከኢትዮጵያውያን ግለሰቦች፣ ይህ ካልተሳካም ከአፍሪካዊም ሆነ ከአለም አቀፍ ተቋማት፣ ወይም ከአፍሪካና ከሌሎች ወዳጅ አገሮች፣ ወይም አለም አቀፍ እውቅና ካላቸው ግለሰቦች የተመረጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አደራዳሪዎቹ በተቻለ መጠን በሁሉም ተደራዳሪ ወገኖች ተቀባይነት ያገኙ ሊሆኑ ይገባል፡፡

ሠ. በተኩስ ማቆሙ ስምምነት የድርድር ሂደት ላይ መሳተፍ የሚገባቸው አካላት የፌዴራሉ መንግስት፣ የአማራ ክልላዊ መንግስት፣ የትግራይ ክልላዊ መንግስት፣ የአፋር ክልላዊ መንግስት፣ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስትና በአገር ውስጥ በትግል ላይ የሚገኙና ትርጉም ያለው የታጠቀ ሃይል ያላቸው አማጽያን ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አማጽያኑ የሚገኙባቸው ክልላዊ መንግስታትም በድርድሩ ሂደት ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ (ለምሳሌ የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊትና የኦሮሚያ ክልል መንግስት በዚህ አግባብ የድርድሩ ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ እንደማለት ነው)፡፡

ረ. ተፋላሚ ሀይሎች ተደራዳሪ ለመሆን የተቀመጠውን መስፈርት ስለማሟላታቸው የማጣራቱ ሃላፊነት የአደራዳሪ ወገኖች ሊሆን ይገባል፡፡ እነዚህ ተፋላሚ ወገኖች እያንዳንዳቸውን በሚመለከቱ አጀንዳዎች ብቻ በተናጠል ወይም በጋራ ከማን ጋር መደራደር እንዳለባቸው የሚወሰነውም በአደራዳሪው አካል ሊሆን ይገባል፡፡

ሸ. የተኩስ ማቆሙ ስምምነት በሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል፤

ሸ. 1. ጦርነት በተካሄደባቸው አካባቢዎች ለህዝቡ ሰብአዊ እርዳታና መሰረታዊ አገልግሎት እንዴት በፍጥነት መዳረስ እንደሚገባው፤

ሸ. 2. የሽግግር መንግስት እስኪቋቋም ድረስ አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታ እንዴት መስፈን እንደሚችል፤

ሸ. 3. ተፋላሚ ወገኖችና ደጋፊዎቻቸው በምን አግባብ እርስ-በእርስ መከባበር፣ እንዲሁም ከጥላቻ ቅስቀሳና ንግግር መቆጠብ እንዳለባቸው፤

ሸ. 4. በጦርነቱ ወቅት የተፈጸሙ ወንጀሎች በገለልተኛ ሃይል እንዴት መጣራት እንዳለባቸውና ወንጀል ፈጻሚዎቹም እንዴት በህግ ተጠያቂ እንደሚሆኑ፤

ሸ. 5. የተኩስ ማቆም ስምምነት በተደረገ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አንድ አገራዊ የውይይትና የድርድር ሂደት አስፈጻሚ ኮሚሽን እንዴት መቋቋም እንደሚችል፤

ሸ. 6. የተኩስ ማቆም ስምምነት በተደረገ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ በምን አግባብ ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግስት ማቋቋም እንደሚቻል፤

ሸ. 7. ባለፉት ሶስት አመታት ከፖለቲካ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የታሰሩ ሰዎች ከእስር ስለሚፈቱበትና ያለአግባብ እገዳ የተጣለባቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ትግሉ መመለስ ስለሚችሉበት ሁኔታ፤

ሸ. 8. የሚቋቋመው የሽግግር መንግስት በክልሎች መካከል ለተነሱ የግዛት ይገባኛል ጥያቄዎች ዘላቂ መፍትሄ እስከሚያበጅ ድረስ አወዛጋቢዎቹ አካባቢዎች በምን ሁኔታ መቆየት እንደሚኖርባቸው፤

ሸ. 9. የውጭ አገራት ታጣቂ ሀይሎች በምን ሁኔታ አገሪቱን ለቀው መውጣት እንዳለባቸው፤

ሸ 10. ተፋላሚ ወገኖችን ወክለው በድርድሩ ሂደት ተሳታፊ የሚሆኑ የፖለቲካ ሰዎች ለደህንነታቸው አስተማማኝ ዋስትና ስለሚያገኙበት ሁኔታና ስለሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ዝርዝር ስምምነቶችን ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 4. አገራዊ የድርድርና የውይይት ሂደት (National Dialogue) ለማካሄድ የሚያስችል ገለልተኛ ኮሚሽን በማቋቋሙ ሂደት ላይ ታሳቢ ሊሆኑ የሚገባቸው ጉዳዮች

አገራዊ የውይይትና የድርድር ሂደት አሳታፊነትን፣ የሁሉን አቀፍነትን፣ የግልጽነትንና የውጤት ተኮርነትን መርሆዎች መሰረት ባደረገ አግባብ በሰከነ ሁኔታ መካሄድ ያለበት ውስብስብ ሂደት ነው። አሁን በአገሪቱ ከሚታየው እጅግ አሳሳቢ ፖለቲካዊ ሁኔታ አኳያ ብልፅግና ፓርቲ የራሱን የበላይነት ጠብቆ በቅርቡ ሊያካሂደው ባሰበው መንገድ ውጤታማ አገራዊ የድርድርና የውይይት ሂደት ሊካሄድ አይችልም። እንዲህ አይነቱን ወሳኝ ሂደት በብቃት ለማካሄድ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን መርሆች የተከተለ አንድ አገር አቀፍ ኮሚሽን ማቋቋም ያስፈልጋል። የሚቋቋመውን ኮሚሽን በተመለከተ ቢያንስ የሚከተሉትን ነጥቦች ታሳቢ ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል።

ሀ. ከሲቪክ ማህበራት፣ ከሀይማኖት ተቋማት፣ ከምሁራንና ከባለሙያዎች እንዲሁም ሰፋ ያለ ማህበራዊ መሰረት ካላቸው ገለልተኛ ዜጎች የተውጣጣ አንድ አገራዊ የድርድርና የውይይት ሂደት አስፈጻሚ ኮሚሽን እንዲቋቋም ይደረጋል፤

(አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የውይይትና የድርድር ሂደቱ በምን አይነት መርሆዎች መመራት እንዳለበት፣ ሊከተላቸው የሚገባ የአሰራር ስልቶችንና ምን አይነት መዋቅር እንደሚኖረው ዝርዝር መነሻ ሃሳብ በኛ በኩል ልናቀርብ እንችላለን)

ለ. ይህ ኮሚሽን የተፋላሚ ወገኖችን የተኩስ ማቆም ስምምነት መሰረት አድርጎ በስልጣን ላይ በሚገኘው መንግስት ፓርላማ አማካይነት በአዋጅ እንዲቋቋም ይደረጋል፤

ሐ. ኮሚሽኑ ምን አይነት አመራር፣ መዋቅርና የስራ ድርሻ ይኑረው ? የሚለውን ጥያቄ ለመወሰን የሚያስችል ሁሉም የአገሪቱ ፖለቲካ ፓርቲዎች በተደራጀ ሁኔታ የሚወከሉበት አገራዊ ጉባኤ አስቀድሞ እንዲካሄድ ይደረጋል፤ ይህንን ጉባኤ የተኩስ ማቆም ስምምነቱን ያደራደሩት አካላት በሃላፊነት ሊያዘጋጁት ይችላሉ፤

መ. የኮሚሽኑ ቀዳሚ ሃላፊነት የተኩስ ማቆም ስምምነት በተደረገ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግስት እንዴት ሊቋቋም እንደሚችል የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማወያየትና ማደራደር ይሆናል፤

ሰ. ኮሚሽኑ በሽግግሩ ዘመን ወቅት የሚካሄዱ የፖለቲካ ድርጅቶችን የድርድር ሂደት፣ ከብሄራዊ መግባባት፣ ከእርቀ ሰላም፤ ከህገ መንግስት ማሻሻያና ከሽግግር ጊዜ ፍትህ ጋር በተያያዘ የሚካሄዱ ህዝባዊ ውይይቶችን በዋናነት የማስተባበር ሃላፊነት ይኖረዋል፤ የአገሪቱ ፖለቲካዊ ችግሮች በሽግግር ዘመኑ ውስጥ ተፈተው የማያልቁ መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግም ኮሚሽኑ ከሽግግር ዘመኑ መጠናቀቅ በኋላም ህልውናው እንዲቀጥል ሊደረግ ይችላል፤

## 5. ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግስት በማቋቋሙ ሂደት ታሳቢ ሊደረጉ የሚገባቸው ዋና ዋና ነጥቦች

በአገራችን በአሁኑ ወቅት ከሚታየው ከፍተኛ የፖለቲካ መካረርና ከችግሮቻችን ክብደት አኳያ የሽግግር መንግስት ማቋቋምና ውጤታማ ስኬት ማግኘት ቀላል ፈተና ሊሆን አይችልም። ሆኖም የገባንበት ውስብስብ ችግር በዚያው መጠን ያለከባድ ፈተና ሊታለፍ አይችልምና ሊከፈል የሚገባውን ዋጋ ሁሉ ከፍለን የሽግግር መንግስት የማቋቋሙን ሂደት ውጤታማ ማድረግ የግድ ይለናል። ውጤታማ የሽግግር መንግስት ለማቋቋምም ቢያንስ የሚከተሉትን መሰረታዊ ነጥቦች ታሳቢ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።

ሀ. የሽግግር መንግስቱ የገዥውንና የተቃዋሚ ፓርቲዎችን የድርድር ውጤት መሰረት አድርጎ አሁን በስራ ላይ በሚገኘው መንግስት ፓርላማ በአዋጅ እንዲቋቋም ማድረግ፤

ለ. የሚቋቋመው የሽግግር መንግስት ከ 20 እስከ 25 በመቶ አሁን በስልጣን ላይ ከሚገኘው ገዥ ፓርቲ፤ ከ 20 እስከ 25 በመቶ አንድነት ወይም ዜግነት ተኮር ከሆኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፤ ከ20 እስከ 25 በመቶ ብሄር ተኮር (በብሄር ከተደራጁ) ከሆኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፤ ከ25 እስከ 40 በመቶ ከሲቪክ ማህበራትና ከተለያዩ የህብረተሰብ ወኪሎች (ዳያስፖራውን ጨምሮ) በተውጣጡ አካላት ውክልና እንዲቋቋም ማድረግ ይቻላል፡፡ እነዚህ አራት የሽግግር መንግስቱ ታሳታፊ ኅራዎች በምን አግባብ በተደራጀ ሁኔታ ወኪሎቻቸውን መምረጥ እንደሚገባቸው የሚያሳይ ግልጽ አሰራር አስቀድሞ እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በሽግግር መንግስቱ ውስጥ ገዥው ፓርቲ ብቻውን ከ20 እስከ 25 በመቶ፣ ሌሎች አካላት ደግሞ ከ75 እስከ 80 በመቶ ድርሻ እንዲኖራቸው ማድረግ የሚያስፈልገው የሽግግሩ ሂደት ህጋዊ ተቀባይነትንና ህዝባዊ ቅቡልነትን በአግባቡ አጣምሮ እንዲገኝ ታስቦ መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ከሲቪክ ማህበራትና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ከ25 እስከ 40 በመቶ የሚል ሰፊ የድርሻ ማእቀፍ እንዲኖር የተደረገውም በተጨባጭ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችል ሁኔታ ከተገኘ የእነሱን ተሳትፎ የበለጠ ማስፋት ጠቃሚ ይሆናል ተብሎ ስለታመነ ነው። በተጨማሪም በስልጣን ላይ ያለውን ብልጽግና ፓርቲ አቋም በመረዳት ረገድ የአንድነት ሃይል ነኝ የሚለው ጎራ እንደ ብሄርተኛ ድርጅት፣ ብሄርተኛ ነኝ የሚለው ጎራ ደግሞ እንደ አሃዳዊ ሃይል የሚያዩት በመሆኑ ምክንያት ይህ ከፍ ሲል የተቀመጠው ቀመር አከራካሪና የፖለቲካ ሃይሎች ዋና የድርድር አጀንዳ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

ሐ. የሽግግር መንግስቱን የስራ ዘመን ከሁለት አመት ያላነሰና ከሶስት አመት ያልበለጠ እንዲሆን ማድረግ፤ የሽግግር ጊዜው ረዘም ያለ እድሜ እንዲኖረው የሚያስፈልገው ጊዜው የሽግግር መንግስቱን ሃላፊነቶች ለመወጣት ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ፓርቲዎች የመደራጃና የመዘጋጃ ወቅት ጭምር እንዲሆን ታስቦ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

መ. የሽግግር መንግስቱ የራሱ ቻርተር፣ የህግ አውጪ ሸንጎና የተለያዩ የስራ አስፈጻሚ ዘርፎች እንዲኖሩት አድርጎ ማደራጀት፤ የሽግግር ዘመኑ ቻርተር ከሚተካቸው ውስን የህግ ድንጋጌዎችና ተቋማት በስተቀር በስራ ላይ ያለውን ህገ መንግስት ጨምሮ ሁሉም የአገሪቱ ህጎችና መዋቅሮች በስራ ላይ እንዲቀጥሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ይህን ማድረግ አስፈላጊ የሚሆነውም በአንድ በኩል የሽግግር ሂደቱ ሁሉን ነገር አፍርሶ ከዜሮ የሚጀመር ስር-ነቀል ለውጥ አለመሆኑን ለማሳየት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለሽግግር ሂደቱ ስምረት ተብለው በማዕከል ደረጃ ከሚፈጠሩ ተቋማትና ከሚወጡ ህግጋት በስተቀር በህዝብ ውሳኔ እስኪሻሻል ድረስ የወቅቱ ህገ-መንግስትም ሆነ ልዩ ልዩ የመንግስት መዋቅሮች የሽግግሩ ወቅት ህግጋትና መዋቅሮች ሆነው እንዲቀጥሉ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ለማሳየት ነው።

ሠ. በሽግግር ዘመኑ ወቅት የሚካሄደው የሽግግር ጊዜ ፍትህ (Transitional Justice) ሂደትና አሰራር ህጋዊ ተጠያቂነትን፣ እርቅንና ይቅርታን ሚዛን በጠበቀ መርህ እንዲፈጸም ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ረ. የሽግግር መንግስቱ የሚከተሉት ዋና ዋና የስራ ሃላፊነቶች ሊኖሩት ይገባል።

ረ. 1. የተኩስ ማቆም ስምምነቱን በዘላቂነት ማስፈጸም፤

ረ. 2. በጦርነቱ ወቅት ውድመት የደረሰባቸውን ክልሎች፣ ከኑሯቸው የተፈናቀሉና በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን ዜጎች እንደገና ማቋቋም፤

ረ. 3. ብሄራዊ እርቅና የሽግግር ጊዜ ፍትህን ማስፈን፤

ረ. 4. በጦርነቱ ወቅት የተዳከመውን የአገሪቱን መከላከያ ሰራዊትና ልዩ ልዩ የፀጥታ ተቋማት የተፋላሚ ወገኖችን ሰራዊትና የክልል ሃይሎችን በሚያሳትፍ አግባብ እንደገና ተጠናክሮ እንዲቋቋም ማድረግ፤

ረ. 5. በመላ አገሪቱ አስተማማኝ ሰላምና የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ማድረግ፤ በተለይም ኢትዮጵያውያን ዜጎችን በብሄርና በሃይማኖት ማንነታቸው የማጥቃት፣ የማፈናቀል፣... ወዘተ ተግባራትን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንዲቆም ማድረግ፤

ረ.6. በጦርነቱ ምክንያት የተዳከመውን ኢኮኖሚ እንደገና እንዲያንሰራራ ማድረግ፤

ረ. 7. የኢትዮጵያ አንድነት፣ ሉዓላዊነትና ዳር ድንበር እንዲሁም የግለሰብና የቡድን መብቶችም ሆነ ማንነቶች በአግባቡ እንዲከበሩ ማድረግ፤

ረ. 8. በዋና ዋና ፖለቲካዊ ቅራኔዎች ዙሪያ አገራዊ መግባባት መፍጠር በሚያስችል ሁኔታ በእውነተኛና ቀጥተኛ የህዝብ ውሳኔ ህገ መንግስታዊ ማሻሻያ የማድረግና በህገ መንግስታዊ ማሻሻያው አማካይነት የአስተዳደር ወሰንና የአስተዳደር እርከን ለውጥን ለሚመለከቱ የህዝብ ጥያቄዎች ተገቢና ዘላቂ መፍትሄ መስጠት፤

ረ. 9. ግልጽነት ያለው የህዝብ ቆጠራ ማካሄድ፤

ረ. 10. በመጨረሻም ነጻና ፍትሃዊ የሆነ አገራዊ ምርጫ በማካሄድ የሽግግር መንግስቱን ስልጣን በህዝብ ለተመረጠ መንግስት ማስረከብና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን ማስፈጸም ይሆናል፡፡

ሸ. የሽግግር መንግስቱ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ሀላፊነቶች ለመወጣት የሚያስችሉ የሚከተሉት ዋና ዋና መዋቅሮች ሊኖሩት ይችላሉ። እነሱም:-

=> የሽግግር ብሄራዊ ሸንጎ (የአገሪቱን ፓርላማ የሚተካ)፤

=> የፌዴራልና የክልል የስራ አስፈጻሚ ካውንስሎች፤

=> የሚኒስትሮች ካቢኔ፤

=> የብሄራዊ ደህንነት አስተባባሪ ኮሚሽን፤

=> የብሄራዊ መግባባት አስተባባሪና የህገ መንግስት ማሻሻያ ሃሳብ አቅራቢ ኮሚሽን፤

=> የእርቀ ሰላምና የሽግግር ጊዜ ፍትህ አስፈጻሚ ኮሚሽን፤

=> የክልሎች የሽግግር አስተባባሪ ኮሚሽን፤

=> የምርጫና የህዝብ ቆጠራ አስፈጻሚ ኮሚሽን፤ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 6. የሚቋቋመው የሽግግር መንግስት ከ 1983 ዓ. ም. የሽግግር ሂደት ግድፈቶች በመማር ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ነጥቦች

የሚቋቋመው የሽግግር መንግስት ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ የ1983 ዓመተ ምህረትን የሽግግር ሂደት ጠንካራና ደካማ ጎኖች በጥልቀት መገመገምና ጠቃሚ ተመክሮ አስቀድሞ መውሰድ ጠቃሚ ይሆናል። በ1983 ዓ.ም. በአገራችን የተካሄደው የሽግግር ሂደት የታዩበት ድክመቶች እንዳይደገሙ ለማድረግም በሚከተሉት ነጥቦች ዙሪያ ልዩ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ይሆናል።

ሀ. የሽግግር ሂደቱ ማንኛውንም የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ የህብረተሰብ ክፍል በማያገልበት ሁኔታ “በሁሉን አቀፍነት” መርህ እንዲካሄድ ማድረግ፤

ለ. የሽግግር ሂደቱ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ጎራ የተለየ ተጽእኖ በማይፈጥርበት አግባብ እንዲካሄድ ማድረግ፤

ሐ. የሽግግር ሂደቱ ሁሉንም ነገር አፍርሶ በመገንባት ሳይሆን ባለው ላይ የመጨመርን አሰራር በተከተለ አግባብ እንዲካሄድ ማድረግ፤

መ. የሽግግር ሂደቱ ለህዝብ ግልጽነት ባለውና ህዝብን በስፋት የሂደቱ ተሳታፊ ባደረገ አግባብ እንዲካሄድ ማድረግ፤

ሰ. የሽግግር ሂደቱ በአገሪቱ ያሉ መሰረታዊ የፖለቲካ ቅራኔዎች ማለትም በቡድንና በግለሰብ መብት፣ የራስን እድል በራስ በመወሰን መብትና በአገር አንድነት መጠበቅ መካከል የሚታዩ ቅራኔዎች አግባብ ባለው ሚዛን እንዲቻቻሉ ማድረግ በሚያስችል መርህ እንዲካሄድ ማድረግ፤

ረ. በሽግግሩ ወቅት መፈጸም የሚገባው የሽግግር ጊዜ ፍትህ ከበቀልና ከጥላቻ በጸዳ መንፈስ የህግ ተጠያቂነትን፣ እርቅንና ይቅርባይነትን ሚዛን ባስጠበቀ አግባብ እንዲፈጸም ማድረግ፤

ሸ. በሽግግሩ ወቅት የሚቋቋሙ የዴሞክራሲ፣ የፍትህና የፀጥታ ተቋማት ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ተፅእኖ በፀዳ ነጻነትና ገለልተኝነት እንዲቋቋሙ ማድረግ፤

ቀ. በአጠቃላይ የሽግግር ሂደቱ የአገርና የህዝብ ጥቅም መጠበቅን ባስቀደመና ሁሉም የፖለቲካ ሀይሎች የጋራ አሸናፊና ተጠቃሚ በሚሆኑበት አግባብና መርህ እንዲካሄድ ማድረግ ይገባል፡፡

## *መደምደሚያ*

በዚህ የሰላም መነሻ ሃሳብ አቅራቢዎች እምነት የወቅቱ አውዳሚ የእርስ-በእርስ ጦርነትም ሆነ የተወሳሰበው የአገራችን ፖለቲካዊ ችግር ከሰላማዊ የውይይትና የድርድር ሂደት ውጭ ጦርነቱን በማስቀጠል መፍትሄ የማግኘት እድል የለውም። እንዲያውም የጦርነቱ መቀጠል ተጨማሪ የህዝብ እልቂትን የሚያስከትል፣ የአገሪቱን የፖለቲካ ችግር የበለጠ የሚያባብስ፣ የሚያወሳስብና መፍትሄውንም የበለጠ የሚያርቅ ውጤት ያስከትላል።

ህዝባችንን ከተጨማሪ የጦርነትና የረሃብ እልቂት መታደግ የምንችለው፣ አገራችን በቀላሉ ወደማትወጣበት የድህነት አረንቋ እንዳትዘፈቅ ማድረግ የምንችለው፣ የአገሪቱ መከላከያ ሰራዊት ህልውናው ተጠብቆ እንዲቀጥል ማድረግ የምንችለው፣ ያለፉት 30 አመታት የአገዛዝ ስርአት ተቀጻላ የሆነ ማንኛውም የፖለቲካ ሃይል አግባብ ባልሆነ መንገድ እንደገና የስልጣን የበላይነት እንዳያገኝ ማድረግ የምንችለው፣ በህዝቦች መካከል የተፈጠረው አሳሳቢ ቅራኔ መልሶ እንዲጠገን ማድረግ የምንችለው፣ ምናልባትም በአሁኑ ወቅት የሚታየው ውጥረት ረግቦ የትግራይ ህዝብ በራሱ ሙሉ ፈቃድ የኢትዮጵያ አካል ሆኖ የሚቀጥልበትን የተሻለ እድል መፍጠር የምንችለው፣ ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያን ከለየለት የእርስ-በእርስ መተላለቅና መፈራረስ መታደግ የምንችለው አውዳሚውን ጦርነት በማስቀጠል ሳይሆን ጦርነቱን በአስቸኳይ ባለበት በማቆምና ችግሩን በሰላማዊ ውይይትና ድርድር ብቻ ለመፍታት በመወሰን ነው፡፡

ከዚህ በተለየ የጦርነቱ መቀጠል የስልጣን ጥመኞችን ስልጣን ለጊዜው ከማራዘምና የጥላቻ ፖለቲካ አራማጆችን ግላዊና ቡድናዊ ስሜት ከማርካት ባለፈ ለህዝብና ለአገር የሚተርፍ ምንም አይነት ጥቅምና ፋይዳ የለውም፡፡ ይህ የምንገኝበት ውስብስብና መዋቅራዊ የፖለቲካ ችግርም ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግስት ከማቋቋም ባነሰ በሌላ መለስተኛ ጥገናዊ ለውጥ፣ ወይም በስልጣን ላይ በሚገኘው ብልጽግና ፓርቲም ሆነ በህወሃት በሚመራ የፖለቲካ ጎራ አሸናፊነትና የበላይነት በዘላቂነት ሊፈታ የሚችልበት እድልም አይኖርም፡፡

ሁኔታዎች ወደ ኋላ መመለስ በማይችሉበት መጠን ከቁጥጥር ውጭ ሆነው ህዝባችን ለባሰ እልቂት ከመዳረጉና አገራዊ ህልውናችንን እስከወዲያኛው ከማጣታችን በፊት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ ይህንን የሰላም አማራጭ ሃሳብ ሁሉም ተፋላሚ ወገኖች ሊቀበሉትና ለድርድር ሊቀመጡ ይገባል፡፡ ህዝቡም በዚህ ጦርነት የልጆቹን ውድ ህይወት በከንቱ ከመገበርና የአገሩን ህልውና አደጋ ውስጥ ከመጣል ባለፈ እንደ ህዝብ ከዚህ ጦርነት የሚያገኘው ምንም አይነት ጥቅም እንደማይኖር ተገንዝቦ ጦርነቱን ማውገዝና ችግሩ በሰላማዊ መንገድ ብቻ እንዲፈታ በተፋላሚ ወገኖች ላይ የራሱን ጫና መፍጠር ይኖርበታል፡፡ ኢትዮጵያውያን እንደ ህዝብ አርቆ አሳቢነታችን፣ ጀግንነታችን፣ ከሁሉም በላይ ሰላምና አገር ወዳድነታችን በተግባር የሚረጋገጠውም የጦርነት ደጋፊና ተሳታፊ በመሆን ሳይሆን ማንኛውንም አይነት ዋጋ ከፍለን ይህንን አውዳሚ ጦርነት ማስቆም ስንችል ነው፡፡ ይህንን ማድረግ ካልቻልን ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ አገር የለሾች በመሆን በትውልድና በታሪክ ፊት ተጠያቂ መሆናችን አይቀሬ ይሆናል፡፡